Toronto Community Housing

**የSwansea Mews ተከራይ ቦታ ዝውውር**

**ጥያቄዎች እና መልሶች**

**ጁን 14፣ 2022**

---

የቶሮንቶ ማህበረሰብ የመኖርያ ቤትዎች (TCHC) የቶሮንቶ ከተማ ዋና የህንፃ ባለስልጣን ተከራዮችን ለመመለስ አስተማማኝ ለማድረግ ስራው እስኪጠናቀቅ ድረስ Swansea Mewsን ለቀው እንዲወጡ የሰጠውን ትእዛዝ በመከተል ተከራዮችን ለመደገፍ እየሰራ ነው።

ተከራዮች ወደ ጊዜያዊ መጠለያ፣ እንደ ሆቴል ወይም ማደሪያ ዶርም ተዘዋውረዋል ወይም በሂደት ላይ ናቸው። ቀጣዩ እርምጃ ቤተሰቦችን ከዚህ ጊዜያዊ ማረፍያ ወደ የተረጋጋ ተስማሚ ልዩ ፍላጎታቸውን ያሟላ መኖሪያ ቤት ማዛወር ይሆናል። በTCHC ንብረቶች መካከል ለመዘዋወር ከእያንዳንዱ ብቁ ቤተሰብ ጋር የተፈረመው ስምምነት ወደ Swansea Mews የመመለስ መብት ይሰጣል።

ይህ የሚያስከትለውን መስተጓጎል እንገነዘባለን እናም ይህንን ሽግግር በተቻለ መጠን ምቹ በሆነ መንገድ ለማድረግ ጠንክረን እየሰራን ነው።

ወደ የበለጠ ለረጅም ጊዜ የተረጋጋ መኖሪያ ቤት የመዘዋወር ሂደት (ለግንባታ ስራው ጊዜ) ቀድሞ በነበረው የTCHC የመዘዋወር ፖሊሲ ላይ የተመሰረተ ሂደትን ይከተላል። በምርጫ ወረፋ፣ በመኖርያ ምርጫ ሂደት፣ በአቅርቦት እና ሌሎችም ውስጥ ለቤተሰብዎች ቦታን በዘፈቀደ እጣ ማውጣትን ያካትታል።

## 1) የዘፈቀደ እጣው እንዴት ነው የሚሰራው?

የእጣው ሂደቱ በWebex በኩል ይካሄዳል። ሁሉም የSwansea Mews ተከራዮች የቀጥታ ስርጭቱን መመልከት ይችላሉ። ሁሉም የቤት አድራሻዎች (ለግላዊነት ሲባል ስሞች ጥቅም ላይ አይውሉም) ለእጣ የሚውለው ሳጥን ውስጥ ይደረጋሉ። አድራሻዎች ከሳጥን ውስጥ ይወጡና ከእጣ ቁጥራቸው ጋር በቀጥታ ስርጭት ይነበባል።

## 2) ለዝውውሩ ምን ያክል መኖርያዎች ነው ያሉት?

TCHC በንብረቶቹ ውስጥ ካሉት ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ነገሮች ሁሉ በላይ ለSwansea ዝውውር ቅድሚያ እየሰጠ ነው። መኖርያዎቹ ክፍት ሲሆኑ፣ ለዚህ ሂደት የምናቆያቸው ይሆናል። አዳዲስ መኖርያዎች በየቀኑ ይኖራሉ።

### 3) የምርጫው ሂደት እንዴት ነው የሚሰራው?

ከእጣው ሂደት በኋላ፣ TCHC እርስዎ ብቁ የሆኑባቸውን መኖርያዎች ዝርዝር ይሰጥዎታል። ዝርዝሩን ለመገምገም እና ውስጣቸው ለመግባት ፈቃደኛ የሆኑባቸውን መኖርያዎች ለመምረጥ ጊዜ ይኖርዎታል። በምርጫ ቅጹ ላይ እነዚህን መኖርያዎች እንደ ምርጫዎ ቅደም ተከተል ያስቀምጣቸዋል። እርስዎ ውስጡ ለመግባት ፈቃደኛ የሆኑበትን የቻሉትን ያህል መኖርያዎችን እንዲዘረዝሩ እናበረታታዎታለን። ይህ በፍጥነት ከሆነ መኖርያ ጋር የመጣመር እድሎዎን ይጨምራል።

### 4) የዘፈቀደ እጣው ላይ በጣም ትልቅ ቁጥር ነው የደረሰኝ። ይህ ማለት ከሆነ መኖርያ ጋር አልጣመርም ማለት ነው?

ከሆነ መኖርያ ጋር እስኪጣመሩ ድረስ የTCHC ሰራተኞች ከእርስዎ ጋር ይሰራሉ። የዘፈቀደ እጣ ቁጥሩ ከአንድ በላይ ቤተሰብዎች ተመሳሳይ መኖርያን በሚፈልጉበት ግዜ የመኖርያውን አቅርቦት ማን እንደሚያገኝ ለማወቅ ጥቅም ላይ የሚውል ነው።

> **ምሳሌ፡**- ተከራይ ሀ (እጣ ቁጥር 35) እና ተከራይ ለ (እጣ ቁጥር 47) ሁለቱም 123 Applewood Laneን እንደ መጀመሪያ ምርጫቸው ይመርጣሉ። በዚህን ግዜ ተከራይ ሀ የ123 Applewood Lane አቅርቦትን ይቀበላል። የTCHC ሰራተኞች ለተከራይ ለ ሁለተኛ የመኖርያ ምርጫን ይገመግማሉ እናም ያቀርቡላቸዋል (ዝቅተኛው የእጣ ቁጥር እስካላቸው ወይም ያንን እጣ የመረጡ ብቸኛ ተከራይ እስከሆኑ ድረስ)። ሁሉም ሰው ከመኖሪያው ጋር እስኪጣመር ድረስ ይህ ሂደት ይቀጥላል።

### 5) ያሉትን ክፍሎች ሁሉንም የማልፈልግ ከሆነስ?

ሊገቡበት የሚያስቧቸውን ሁሉንም ክፍሎች በምርጫ ቅፅዎ ላይ እንዲያስቀምጡ እናበረታታዎታለን። ምንም አይነት ክፍሎችን ካልመረጡ ወይም የቀረበልዎትን መኖርያ ውድቅ ካደረጉ፣ ወደ ቀጣዩ ዙር የዝውውር የመኖርያ ማዛመጃ ውስጥ ይካተታሉ። አዳዲስ መኖርያዎች ወደ ዝውውር ክምችት ውስጥ በመደበኛነት

ይመጣሉ፣ ስለሆነም በሚቀጥሉው ዙርዎች የተሻለ የሚመጥንዎት አዲስ መኖርያዎች ሊኖሩ ይችላሉ፣ ምንም እንኳን ይህ እንደሚሆን ለማወቅ ምንም መንገድ ባይኖርም። በዚህ የመጀመሪያ ዙር ለቤተሰብዎ የሚሆኑ መኖርያዎች ካሉ፣ በምርጫ ቅፅዎ ላይ እንዲዘረዝሩ አበክረን እናበረታታዎታለን።

## 6) ልጆቼ አሁን የራሳቸው መኝታ ቤት አላቸው። በአዲሱ መኖርያ ውስጥ የመኝታ ክፍል መጋራት ይኖርባቸዋል?

ልጆችዎ በአሁኑ ጊዜ በSwansea Mews የራሳቸው የመኝታ ክፍል ካላቸው፣ ያንን የመኖሪያ ቤት ክፍሎች መጠን ሲዘዋወሩም ለማግኘት ብቁ ይሆናሉ። ለምሳሌ፣ ባለ ሶስት መኝታ ክፍል መኖርያ ውስጥ ከሆኑ፣ እና ሁለት ሴት ልጆች ካሉዎት እና እያንዳንዳቸው የራሳቸው ክፍል ካላቸው አሁን ላይ፣ እርስዎ ብቁ የሚሆኑባቸው ክፍሎች ዝርዝር ባለ ሶስት መኝታ ክፍሎችን ያካትታል። የመኖርያ ቤትዎች መመዘኛው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ተመሳሳይ ጾታ ያላቸው ሁለት ልጆች ተመሳሳይ የመኝታ ክፍል እንዲጋሩ ስለሚፈቅድ እርስዎ ብቁ የሚሆኑባቸው መኖርያዎች[1] ዝርዝር ባለ ሁለት መኝታ ቤቶችንም ያካትታል። ባለ ሁለት መኝታ እና ባለ ሶስት መኝታ የመኖርያ ምርጫዎች ይኖርዎታል። ያለዎትን አማራጮች ስለሚያሰፉ እና ቶሎ ለመልቀቅ ስለሚያስችልዎ የቤተሰብዎን ፍላጎት ለሚያሟሉ ትናንሽ መኖርያዎች እራስዎን ክፍት እንያደርጉ እናበረታታዎታለን።

## 7) አነስ ያለ የዝውውር መኖርያን ከተቀበልኩ ወደ Swansea Mews ስመለስ ትልቅ መጠን ወዳለው መመለስ እችላለሁን?

አዎ፣ ትልቅ መጠን ላለው መኖርያ ብቁ እስከሆኑ ድረስ ወደ Swansea Mews ሲመለሱ ወደ ትልቁ መኖርያ መግባት ይችላሉ። ከላይ ላለው ምሳሌ፣ ሁለቱም ሴቶች ልጆችዎ የቤተሰብዎ አባላት ሆነው ከቀጠሉ ባለ ሶስት ክፍል መኖርያ ለማግኘት ብቁ ሆነው ይቆያሉ።

---

[1] ግልፅ ለማድረግ ጾታ የሚከተሉትን ያጠቃልላል:- ወንድ፣ ሴት፣ ጾታ የቀየረ ወንድ፣ ጾታ የቀየረች ሴት፣ ሁለትዮሽ ያልሆኑ፣ ሁለት መንፈስ፣ ያልተዘረዘሩ እና ያለመመለስን እመርጣለው።

**8) ከተስካከለ በኋላ ወደ Swansea Mews እንድመለስ እንደምትፈቅዱልኝ እንዴት አውቃለሁ?**

TCHC ከእርስዎ ጋር የቦታ ዝውውር ስምምነት ይፈርማል። ይህ በእርስዎ እና በTCHC መካከል የሚኖር ህጋዊ ስምምነት ሲሆን ወደ Swansea የመመለስ መብትዎን ይገልፃል። ከመፈረምዎ በፊት የራስዎ የህግ አማካሪ ስምምነቱን እንዲመለከት የሚፈልጉ ከሆነ፣ እንዲያደርጉት እናበረታታዎታለን።

**9) የቤት ኪራይ ይጨምር ይሆን?**

የRGI ተከራይ ከሆኑ የቤት ኪራይዎ በRGI ደንቦጭ መሰረት መሰላቱ ይቀጥላል።

**10) የመኖርያ ምርጫዎቼ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መወሰን ይኖርብኛል?**

ይህ የዝውውር ሂደት በፍጥነት ነው እየተካሄደ ያለው ምክንያቱም በተቻለ ፍጥነት እርስዎን ከዝውውር መኖርያዎ ጋር እንዲጣመሩ ስለምንፈልግ ነው። ብቁ የሆኑባቸውን መኖርያዎች ዝርዝር ይደርስዎታል ከዚያም ለመምረጥ እና እንደ ምርጫዎ ቅደም ተከተል በዝርዝር ለማስቀመጥ አራት ቀናት ይኖሩዎታል።

**11) ምርጫዎቼን ደረጃ ከመስጠቴ በፊት የምፈልጋቸውን መኖርያዎች መጎብኘት እችላለሁ?**

ከፈለጉ የሚፈልጓቸውን የመኖርያ ማህበረሰቦችን መጎብኘት ይችላሉ ነገር ግን በሚያሳዝን ሁኔታ ምርጫዎችዎን ከማስገባትዎ በፊት ወደ መኖርያዎቹ መጎብኘትን ልናስተባብር አንችልም። ስለሚፈልጓቸው መኖርያዎች እንዲሁም ማህበረሰቦች በተመለከተ ስለሚኖርዎት ጥያቄዎች የTCHC የዝውውር ሰራተኞች መልስ ለመስጠት ይገኛሉ።

12) **የቀረበልኝን መኖርያ ከመቀበሌ በፊት የቀረበልኝን መኖርያ መጎብኘት እችላለሁን፣ በተለይም የመኖርያውን ውስጡን ለማየት?**

አዎ። አንዴ የመኖርያ አቅርቦትን ከተቀበሉ ውሳኔ ከማድረግዎ በፊት ያንን መኖርያ ለማየት እና ለመጎብኘት እድል ይኖርዎታል።

**13) የቀረበልኝን መኖርያ ካልተቀበልኩ ምን ይሆናል?**

የቀረበልዎትን መኖርያ ውድቅ ካደረጉ፣ ወደ ቀጣዩ ዙር የምርጫ ሂደት እንዲገቡ ይደረጋሉ። ሌላ ብቁ የሆኑባቸው መኖርያዎች ዝርዝር ይሰጥዎታል እናም እንደገና በምርጫ ሂደቱ ውስጥ ያልፋሉ።

**14) ውዝፍ እዳ ካለብኝ ምን ይፈጠራል?**

ውዝፍ እዳ ካለብዎት እና ከTCHC ጋር የክፍያ ስምምነት ከሌለዎት ውዝፍ እዳውን ለመክፈል ስምምነት ማድረግ ያስፈልግዎታል። የተከራይ አገልግሎት አስተባባሪዎ በዚህ ሂደት ላይ ሊረዳዎ ይችላል።

**15) ባለ ሶስት መኝታ መኖርያ ነው ያለኝ፣ ነገር ግን ልጆቼ ከቤት ወጥተዋል እናም አሁን ብቻዬን ነው የምኖረው። ወደ አዲስ ባለ ሶስት መኝታ መኖርያ መግባት እችላለሁ?**

ከእርስዎ ጋር ለሚኖሩ ሰዎች የበዛ መኝታ ቤቶች ያሉት መኖርያ ወስጥ መኖር ትርፍ ቤት መያዝ ይባላል። የRGI ቤተሰብ ከሆኑ እና ትርፍ ቤት የያዙ ከሆኑ፣ ብቁ የሚሆኑባቸው መኖርያዎች ዝርዝር አሁን ባለዎት የቤተሰብ መጠን ላይ የተመሰረተ ይሆናል። በዚህ ሁኔታ፣ ለባለ አንድ መኝታ መኖርያ ብቁ ይሆናሉ። ሁሉም የRGI ቤተሰቦች ወደ ሌላ መኖርያ ሲቀይሩ ትክክለኛ መጠን ያለው እንድንሰጣቸው በቤቶች አገልግሎት ህግ እንገደዳለን።

**16) ለአድራሾች መክፈል ይኖርብኛል?**

በSwansea Mews የሚገኘውን ቤትዎን ለቀው ሲወጡ እንዲሁም ከጥገና ወይም እንደገና ግንባታ በኋላ ወደ ማህበረሰቡ ለመመለስ TCHC የአድራሽ ወጪዎችዎን ይከፍላል። ነገር ግን እኛ ከቤተሰብ መጠናቸው በላይ የሆነ መኝታ ቤታ ያለው መኖርያ (ትርፍ ቤት መያዝ) ያላቸውን ቤተሰቦች ወደ Swansea Mews የመመለስ ወጪን አንከፍልም።

ስለ ወደ ሌላ ቦታ የመዘዋወር ሂደት የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎን በስልክ ቁጥር **416-945-0900** ወይም በኢሜል Swansea.Mews@torontohousing.ca ያናግሩን።

********